# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው - ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
All ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)

38ኛ ዓመት | ቁጥር 1 | መስከረም 2005


## ድህረ መለስ ኢትዮጵያ
## ቀጣይ ሥርዓት - ቀጣይ የጥፋት አዙሪት

በቅድሚያ ላለፉት 21 ዓመታት ኢትየጵያን በገዙት አቶ መለስ ዜናዊ እረፍት ለቤተሰቦቻቸውና ለቅርብ ወዳጆቻቻው መፅና ናትን እንመኛለን።

በአቶ መለስ ሕልፈት ምክንያት "ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዴት?" የሚለው ጥያቄ እየተነሳ በተለይ ደግሞ ከእንግዲህ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ፖለቲካ ምሕዳሩን "ከፈት" ለማድረግ ይሞክራሉ ወይስ ከአፋኝና አሸባሪ ስርዓታቸው በስተቀር ምንም አማራጭ የለንም ብለው ይገፉበታል? የሆነ ቢሆን ከዚህ አዲስ ሁኔታ አንጻር የሃገራችን ዴሞክራቶች ለቀጣዩ ትግል እንዴት ይዘገጃ? ወዘተ በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ በርከታ ውይይቶችና ክርክሮች እየተካሔዱ ነው። ለነዚህ ጥያቄዎች ትግል አጋዥ የሆነ መልስ ለመስጠት ከፈለግን፣ ከሁሉ አስቀድሞ በመለስ ዜናዊ መሪነት የተተከለውን፣ ከሱም እልፈት በሁዋላ የወያኔ/ኢ.ሕአዴግ መሪዎች ከኛም አልፎ ለቀጣዩ ትው ልድ ይጸናል የሚሉት ስርዓት እጅግ አስከፊ የሆነ የጥፋት አዙሪት ገጽታ እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል። ምን ዓይነት የጥፋት አዙሪት?

ከሁሉ ከሁሉ በፊት የዚህ አገዛዝ ውድቀትና የችግራችን ሁሉ ምንጭ የሆነው በአመት ከአስር በመቶ በላይ "ዕድገት" ተመዘገበ እየተባለ ሌት ተቀን ከሚለፈፈው ፐሮፓጋንዳ በተ ጻራሪ ከሀገራችን ሕዝብ አብዛኛው የሚገኝበት ዘግናኝና ከዓመት ዓመት እየከፋና እየሰፋ በመሄድ ላይ ያለው ማጣትና ድህነት ነው። ይህ የህዝበችን የሰቆቃ ኑሮ የሚለካው የተባበሩት መንግሥታትም ሆነ በሌሎችም አለም አቀፍ ተቋማት ከአመት አመት የሚወጡት በድህትና በኑሮ ጉስቁልና ዙሪያ የሚቀርቡ ሪፖረቶች ኢትዮጵያን በዓለም ከመጨራሻዎቹ አምስት አገሮች አንዷ አድርገው በማስቀመጣቸው ብቻ አይደለም። ይባስ ተብሎ በእነዚሁ ጥናቶች በእድገትና በህዝብ ኑሮ መደላደል ሰላለው ዝምድና ሲወሳ ከእድገት ጋር የሃብት ድልድልም ፍትሃዊ ሆኖ ድህነትም እየቀነሰ የሄደባቸው በርካታ አገሮች ሲኖሩ፣ ከዚህ በተቃረኒ ደግሞ፣ እድገት ልማትን አየተፃረረና ጠቂቶችን እያከበረ፣ ብዙሃንን ደግሞ ለባሰ ድህነት እየዳረገ የሚሄድባቸው አገሮች ሲወሱ ኢትዮጵያችን ለዚህ አስከፊ ክስተት እንደምሳሌ ጣት የሚቀሰርባት አገር መሆኗ ነው። ይህ ጥቂቶች ሰማይ ጠቀስ ሃብት እያካበቱ ከሌሎቹ አገሮች ከበረቴዎች የማይተናነስ የተንደላቀቀ ኑሮ የሚኖሩበት፣ ብዙሃን ደግሞ ካምናው ዘንድሮ እየከፋ ለሚሄድ ሰቆቃ የሚዳረጉበት ክስተት ሚሊዎኖች በእለት ከእለት ኑሯው የሚያዩት ሃቅ ነው። ወያኔ/ኢህአዴግ የዛሬ 21 ዓመት ዋና አላማዬ እትዮጵያውያን በቀን ሶስቴ በልተው እንዲያድሩ ነው በሚል "ረሃብ ቆይ ብቻ! ቆይ ብቻ!" እያለ ሲሰነዝር የቆየው "ዛቻ" አንፃር ሶስቴው ቀርቶ አንዴም አሮበት ህዝብ የበይ ተመልካት በሆነባት አገር በዚህ መልክ የባዕዳንን ወይም የሃገር ምሁራንን ጥናቶቾ መጥቀሱ ለቀባሪ ማርዳት ስለሚሆንብን እዚህ ላይ ዝርዝር አንገባም።

የሃገራችን ችግሮች በሙሉ የሚመነጬት በፖለቲከውም፣ በማህ በራዊውም፣ በሰላሙም፣ በሕዝቦች ወንድማማችነትም ሆነ በሀ ገር አንድነቱ መስክ የማንወጣው አስከፊ አዙሪት ውስጥ የጨመረን ይህ በኢ.ሕአዴግ የተተከለው ለጥቂቶች የተገነባና የህዝብ ደም መጣጭ ኢኮኖሚ ስርዓት ነው። ሕዝባችን ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ለመውጣት፣ ዴሞክራሲያዊና ተጠያቂነት የነገሱበት ስርአት ያስፈልገዋል። የወያኔ/ኢ.ሕአዴግ መሪዎች ደግሞ የዚሕ ግፈኛ ስርዓት ዘላቂነት እንዲረጋገጥ፣ በሚለ ፈፈውና በተጨባጭ ሕዝባችን ከሚኖረው ጋር ያለው የከረፋና እየጎላ የሚሄድ ቅራኔ ሊያስነሳ የሚቾልውን ያልሞት ባይ ተጋዳይ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመግታት ከፈለጉ፣ ብዙም አማራጮች የላቸውም። ልክ እንደብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም ከእለት እለት ይባስ የሚረገጡበት፣ አነሱ ሲባሉ የሚቀነሱበት፣ ነገሮች ልክ አይደሉም በሚል የሚነገርና የሚጽፍ እንዳይንዳይኖር፣ የፐሬስ ነጻነት ደብዛው የሚጠፋበት፣ "በቃኝ!" ለማለት የደፈረ ሁሉ ባሸባሪነት የሚፈረጅበት፣ አፋኝና አሸባሪ አገዛዝ የመ ገንባቱን ጉዳይ የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገው ያቀርቡታል። የሕዝብ ትግል አይሎ እነዚህ የጥፋት ሃይሎች ከዚሕ ሂደት እንዲያፈገፍጉ እስከከልተደረገ ድረስ ማጣትና ድህነት እየከፉ ሲሄዱ ሽብርና አፈና እየተባበሱ የምንሄድበት አዙሪት ውስጥ ነን የምንለው ለዚህ ነው፡ እንግዲህ ከዚህ ስንነሳ ሁለት ጥያ ቄዎች ይኖራሉ። አንደኛ የኢትዮጵያ ዲሞከራሲያዊና አገር ውዳድ ሃይሎች እስራቴጂያዊ አላማ ምን መሆን አለበት? ይህንን አላማ እውን ለማድረግ በሚደረገው ታሪካዊ ፍልሚያ ያለው የሃይሎች አሰላለፍ ምን ይመስላል?

እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች የምን ታገለው ለስርዓት ለውጥ እንደሆነ ተብሎ! ተብሎ! ያለቀለት ጉደይ ነው። በዚህ ጉዳይ ሐገራችንና ሕዝባችን የሚያስፈ ልጓቸው ለውጥ ወይም ሽግግር እስካሁን በታሪካችን እንደታየው አንድ ድርጅት ወይም ሃይል አሸንፎና ወይም ተክቶ የራሱን ሥልጣን ለመጫን የሚሞክርበት የኪሳራ ሒደት አይደለም። የሚያስፈልገን ከዚህ እጅግ የሰፋና ሕብረተሰባችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከጸረ ዴሞምራሲ ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ፣ አሸናፊና ተሸናፊ ሳይኖር ሁሉም በአሸናፊነት የሚወጣበት በብሔራዊ ዕርቅ ላይ የተገነባ የሽግግር ሂደት ነው። እንዲህ ዓይነቱን ሕገመንገሥታዊ ሥርአት ለመገንባት አላማ በሀገራችን ዴሞ ክራቶች ጎራ ሰፊ ተቀባይነት ያለው በጎ አካሄድ ነው። ይህንን ሰፊና አገራዊ አጀንዳ ካነገብንና ለዚህ እጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ ለሆነ ታሪካዊ ተጋድሎ እራሳችንን ብቁ ለማድረግ ከፈለግን፣ ከሁሉ በፊት በዚህ ፍልሚያ ያለው የሃይል አሰላለፍ እንዴት ነው? ከዚያ ደግሞ ከዚህ አሰላለፍ አንጻር የመለስ ዜናዊ ሕልፈት ምን የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልከት ያስፈልጋል።

የወያኔ/ኢህአዴግን ሰፈር በተመለከተ፣ እነሱ እንደሚሉትና አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ "በእንባ ጎርፍ እያጀበ አሳየ" እንደሚባለው ሕዝባችን ከዳር እስከዳር የሚደግፉቸው አይደ ሉም። አንዳንድ ተቃዋሚዎች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ደግሞ፣ ይህ ሃይል በህብረተሰቡ ውስጥ ማንንም የማይወክል፣ ከሕብረተሰቡ በሙሉ የተነጠለ፣ ምንም መሰረት የሌለውና ገፍተር ቢያደረጉት ሊወድቅ የሚችል ሃይል አይደለም። ወያኔ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ከአዲስ አበባ እስከ ዳር ድንበር መንደር፣ ሌላው ቀርቶ በቤተሰብ ደረጃ ድረስ የወረደ የተዋቀረ ሃይል ነው። በለፉት 21 ዓመታት፣ በተለይ ደግሞ ከግንቦት 97 ወዲህ ባደረገው ደጋፊ የመሰብሰብና የማደራጀት ጥረት የተነሳ፣ ዛሬ በተለይ ከወጣቱ የተወሰነ ሃይል መልምሎና አደራጅቶ ለሥርዓቱ ተናካሽ ወይም ቮካል የሆነ፣ ጥቅሙን

የሚያውቅ ትኩስ ሃይል አፍርቷል። እንደመንግሥት ሆኖ ደግሞ በሰራዊቱ፤ በመንግሥት በጀት፤ በፖሊሱ፤ በመረጃ መረቡ፤ በመገናኛ ብዙሃን ላይ በብቸኝነት ባለው ቁጥጥር ይጠቀማል። ከዚህ አልፎም በተከለው የመሬት ስሪት አማካይነት በደርዘን ሚሊዮን ገበሬዎች ህልውና ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን አለው።

ከዚህ ድርጅታዊና መንግሥታዊ አቅም አንፃር የተቃዋሚውን ጎራ ብንመለከት፤ ከወያኔ/እህአዴግ የጥንካሬ ምንጮች አንዱም እንደሌለው እናያለን። በምንም ምክንያት ይሁን በምን የወያኔ/ኢህአዴግ ድርጅታዊ መዋቅርም፤ ጥንካሬም፤ አቅምም የለውም። ያለው የማይበገር ሃይል እነሱ ሊደርሱበት የማ ይችሉት ሕዝባዊ ሃይል ብቻ ነበር። ነገር ግን እራሳችንን እናታልል ከላልን በስተቀር፤ ዛሬ ሕዝባችንን ከዳር እስከ ዳር አንቀሳቅሰን የትግሉ ማዕከልና የበጎ ለውጥ አራማጅ ሃይል ለማድረግ የምንችልበት ሁኔታ ውስጥ አይደለንም። በተለይ በግንቦት 97 ማግስት በተደጋጋሚ የተፈጸሙ ስህተቶች፤ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ሕዝባችንን የትግሉ ማዕከል ለማድረግ የምንከተ ላቸውና የጨበጥናቸው መፈክሮች ለሕዝባችን ተጨባጭ የሰቆቃ ኑሮ አማራጮች ከማቅረብ ይልቅ "ራዕይ ነክ" የሆኑ መፈክሮች ናቸው። በዚህም ምክንያት በሕዝባችን ዓይን በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ንቀትን የተላበሰ የተአማኒነት ችግር አለ ብን።

በዚህ ጉዳይ ከሁለት ዓመት ተኩል በፊት፤ የኢትዮጵያ ዴሞ ክራሲያዊ ሕብረት (ኢዴሃሕ) የተቃዋሚ ጎራ ያጣውን ተአማኒነት መልሶ እንዲያገኝ፤ ከዚያም በሁዋላ ደግሞ፤ የተቀ ሰቀሰው ሕዝባዊ ትግል በወያኔ/ኢህአዴግ የአፈናና የከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ ሳይበተን ቀጣይነት እንዲኖረው ምን ማድረግ ይጠበቅብናል በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ሰፊ ትንተና አቅ ርበናል። ይህንን "ለሕዝባዊ ትግል ማዕበል ብቃት ያለው ሕብ ረተሰብ፤ ብቃት አልባ አመራር" በሚል ርዕስ መጋቢት 2002 ዓ.ም. ያወጣነውንና በተላያዩ ድህረገጾች ለንባብ የበቃ ሰፊ ትንተና አንባቢ እንደገና እንዲመለከተው እንጋብዛለን።[1]

በመለስ ዜናዊ ሕልፈት ምክንያት በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከቀረ ቡት ትንተናዎችና ለሥርዓት ለውጥ ተግላችን ከተጠቆሙት አካሄዶች ሌላ የምንጨምረው ነገር አይኖርም። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፤ ከዚህ ተያይዞ ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው አዙሪት አንጻር ምን የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ሰሞኑን ከሚያጎርፉት ልፈፋ ከተነሳን፤ ከነሱ የሚሰጠው አጭርና ግልጽ መልስ ነው። "መለስ ኖረ አልኖረ ቀስ በቀስ የገነባነው ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ ሥርዓት አለ። ይቀጥላል" ባዮች ብቻ አይደሉም። ከዚህም ዘልቀው ሕዝባችን "በነቂስ ወጥቶ" ለመለስ አነባ የተበለውን ክስተት እያጎሉ በማውሳት የዚህ ግፈኛ ስርዓት መቀጠል ከነሱ አልፎ "የሰማንያ ሚሊዎን ሕዝብ ራእይ" መሆኑን ሊያሰምሩን እየሞከሩ ናቸው።

በኛ በኩል ደግሞ ከእንግዲህ አገራችን በዚህ መንገድ ልትቀጥል አይገባም። አትችልምም። ለፖለቲካ እርቅ፤ ለሕግ የበላይነትና ለዴሞክራሲ፤ ለዕውነተኛ ሰላምና ሕዝብን ላካተተ ልማት አዲስ ጅማሮ አዲስ አጋጣሚ ተፈጥሮአል። እንጠቀምበት እንላለን። የፊውዳሉ ስርዓት በየካቲት አብዮት በተደመሰሰ ማግስት፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ የደረግን መንግስት አሸንፎ ስልጣን በያዘ ማግስት፤ ወይም ደግሞ የግንቦት 97 ምርጫ ሲጨነግፍ፤ ለተረጋጋ ሽግግር ላመለጡት ታሪካዊ አጋጣሚዎች ሁኔታ ዛሬም መደገም የለበትም። ለዚህ ደግሞ ይህ የድህነትና የሽብር አዙሪት ተሰብሮ፤ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲተካ፤ በተሳካ የብሔራዊ ሽግግር ሂደት በተረጋጋና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ሕብረተሰባችን ፊቱን ወደልማት እንዲያዞርና ከአስከፊ ድህነት እንዲላቀቅ ለማድረግ ለስርዓት ለውጥ የሚደረገው ትግል መቀጠል ይኖርበታል የሚል ጠንካራ እምነት አለን። ይህ አገራዊ አላማ ግቡን እንዲመታ ከፈለግን ደግሞ ሕዝባችን ባለቤትነት ተሰምቶት በነቂስ ወጥቶ በአንድ አቅጣጫ እንዲታገልና ለድል እንዲበቃ የመጀመሪያ መጀመሪያ "ተነስ ታገል" የሚለውን ጥሪያችንን አምኖ እንዲነቀሳቀስ፤ ቀስ በቀስ ተአማኒነትን የማጎልበት ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። ይህ እራሱ አስቸጋሪ ሊሆን ቢችልም፤ ካለፈው ልምዳችን ትምህርት የቀሰመ አካየሄድ ይኑረን ካልን ደግሞ ሕዝባችን እንደገና ተንቀ ሳቅሶ እንደገና በሽብርና በወያኔ/ኢህአዴግ አይቀሬ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ትጥቅ ፈትቶ የባሰ ጨለምተኝነት ውስጥ እንዳ ይወድቅ ከፍ ተብሎ የተወሳው የኢዴሃህ ሰነድ በተጠቆመው መልክ የትግሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችለን እቅድ አውጥቶ የመንቀሳቀስ ግዴታ ይኖርበናል።

ይህ በዚህ እንዳለ ለሃያ አንድ ረዥም አመታት በሕብረተሰቡ ብቻ ሳይሆን በራሱ በድረጅቱ ውስጥ በአንድ ግለሰብ ዙሪያ ፈላጭ ቆረጭ አገዛዝ ለመገንባት በቅቶ የነበረው የወያኔ/ ኢህአዴግ አመራር ዛሬ ቁንጮውን ማጣቱ በቀጣዩ የትግል ሂደት ምንም ለውጥ አያመጣም፤ መለስና ድህረ መለስ ኢትዮጵያም ሆነች ወያኔ/ኢህአዴግ እንዳሉ ይቀጥላሉ ማለት አይደለም።

የመለስ ዜናዊ ሥርዓት የተገነባው በኢትዮጵያ ሕዝብና በዴሞ ክራሲያዊ ሃይሎች ላይ አፈናና ሽብር እያወረደ ብቻ አይ ደለም። በወያኔ/ኢህአዴግ በራሱም ውስጥ ቢሆን በራዕይና በአካሄድ ልዩነትም ሆነ በስልጣን ሽሚያ የሚነሱትን ግጭቶች፤ የመለስ ዜናዊ አንጃ ሌሎቹን እየመታ፤ እያሰረ፤ እያባረረ፤ ቀስ በቀስ በአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ስር የወደቀ አምባገነናዊ ስርአት ገንብቷል። የግለሰብ አምባገነኖች አነሳስና የሥልጣናቸው ቀጣይነት የሚረጋገጠው፤ አምባገነኑን ሊተካ የሚችል፤ በሁሉም ዘንድ "እሱ ቢያልፍ እገሌ አለ" የሚባል ሌላ ግለሰብ ወይም ሃይል እንዳይኖር በዙሪያቸው የወራሽ ወይም ተተኪ ሃይል ክፍተት ወይም "ቫክዩም" በመፍጠር ብቻ እንደሆነ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ሃቅ ነው። ድህረ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ከዚህ የምታመልጥበት ምንም ተአምር አይኖርም። የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች ለፕሮፓገንዳ ፍጆታ ሲባል ሺ ጊዜ መለስ ዜናዊ "በሰማንያ ሚሊዎን ኢትዮጵያ ተተክቷል"፤ በአመራር ደረጃም ቢሆን፤ "የመተካካቱ" ሂደት በሰከነ ሁኔታ እየተከናወነ ነው ቢሉ ንም በሚቀጥሉት ወራት በአንድ ዘላቂ የሆነ "ሁነኛ" ተተኪ ላይ የመስማማት ችግር እንደሚኖርባቸው ግልጽ ነው። ቀጣዩ ውስ ጣዊ ግብ ግብ ሁለት ዋና ዋና ገጽታዎች ሊኖሩት ይችላሉ።

የመጀመሪያው የዴሞክራሲ ጥያቄ ይሆናል። በአንድ በኩል ሊነሱ ከሚችሉት የሕዝባችን ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችና ሊከሰት ከሚችለው አለም አቀፍ ጫና አንጻር "ትንሽ ከፈት ካላልን የትም አንደርስም" የሚሉና በሌላ በኩል ደግሞ መክፈት ማለት እንደግንቦት 97 በሩ ለጠላቶቻችን የሚበረገድበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል ብለው በለየለት አፈናና ሽብር ከመቀጠል ሌላ አማራጭ የማይታያቸው ወገኖች ይኖራሉ። በዚህ በዴ ሞክራሲ ጉዳይ የሚኖረው ሽኩቻ ከጥቂት መሪዎች ዘልቆ ሊሄድ የሚችልበትም ሁኔታ አለ። በድርጅቱ ውስጥ ባለው ሙሰኝነት የተመረረ፤ "ከበላይ" ግንኙነት ባላቸው ካድሬዎች እየተረገጠ፤ ዕድገትና የኑሮ ሁኔታ በችሎታ ሳይሆን፤ በዘመድ አዝማድና በአምቻ ጋብቻ፤ በሙሰኝነት ሆኖበት አንገቱን የደፋ ካድሬም ቢሆን፤ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ የተሻለ ውስጣዊ ዴሞክራሲና ግልጽነት (ትራንስፓሬንሲ) ብሎ ሊነሳ ይችላል። ሁለተኛ ደግሞ የብሄሮች እኩልነትን የሚመለከት ይሆናል። ማንኛቸውም ቢሆኑ፤ "እንወክላለን" በሚሉት ብሔር ፊት አለን የሚሉት ተቀባይነት ምንም መሰረት የሌለው አባባል ነው። ሆኖም በጥቅም ግጭጦች ሰቢያ በኢሕአዴግ ውስጥ በተለይ ብሔርን አስመልክቶ ከአንዳንድ አይቀሬ ከሚሆኑ ማደናገሪያ "ማሻሻሎች" ዘልቆ በተጨባጭ የተመጣጠነ ውክልና በሚለው ጥያቄ ዙሪያ በአባል ድርጅቶች መሃከል ሌላ ግጭጥ መፈጠሩ አይቀሬ ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች በመለስ ህልፈት ምክንያት ከተፈጠረው አዲስ ሁኔታ አንጻር የትግል ስትራቴጂያችንን ስንቀይስ፤ ከፍ ብለን ሰለ ተአማኒነት ግን ባታ፤ የትግሉን ቀጣይነት ስለማረጋገጥ ግዴታ፤ ህብረተሰባችንን ወደ ዴሞክራሲያዊና በእርቀ ሰላም የተረጋጋ ሽግግር የሚለው ራዕይና አጀንዳ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአጭር ጊዜ ደግሞ ለዚህም አዲስ ክስተት የሚመጥን ታክቲክም እንደሚያስፈልግን ግልጽ ነው። በቀጣዩ ጊዜ ከዚህ አዲስ ሁኔታ ተነስተን ለትግላችን መግፋት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

[1] የመጋቢት 2002 ሰነድ በድህረገጻችን መዝገብ ቤት ቁ.2 ያገኙታል

1. ከዚህ ከመጭው ውስጣዊ ቅራኔና ትንቅንቅ አንጻር “ወያኔ/ኢህአዴግ ወያኔ/እህአዴግ ነው። ትግላችን ይህን የጥፋት ሃይል በሕዝብ ትግል አስገድዶ ዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ መገንባት ስለሆነ ይህ የውስጥ ግጭትና ትግል አይ መለከተንም።” ከሚል አቋም መነሳት የለብንም። “ከፈት እንበል፤ የአባል ድርጅረቶች ብሎም የብሔሮች እኩልነት ይረጋገጥ… ወዘተ እያሉ የሚንቀሳቀሱትን ሃይሎች ከአክራሪዎቹ እኩል ዓይናችሁን ላፈር ማለት አይቻልም። ከዚህ ይልቅ በዚህ 21 ዓመት የተገነባው ጸረ ዴሞክራሲያዊና ዘረኛ ውቅያኖስ መሃል ወያኔ/እህአዴግ ብቻውን ተነጥሎ የዴሞክራሲና የእኩልነት ደሴት ሊሆን የሚችልበት ምንም ተአምር እንደማይኖር እንዲገነዘቡ መጣር ያስፈልጋል። በሐገር የሌለ ዴሞክራሲ በወያኔ/ኢህአዴግ ውስጥ ብቻ፤ ለሃገራችን ብሔሮች የተነፈገ እኩልነት ለዚህ ድርጅት አባሎች ብቻ፤ ሊረጋገጥ የሚችልበት ምንም ዓይነት ተአምር አይኖርም። ከዚህም በመነሳት ትግሉ በዝግ ችሎት እስከተካሄደ ድረስ የትም እንደማያደርስ ተገንዝበው፤ እነዚህ ሃይሎች ዴሞክራሲና የብሔር እኩልነት በመላ ሕብረተሰቡ ይረጋገጥ የሚል አላማ በሕዝብ ፊት መሰለፍ እንዳለባቸው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከጎናቸው እንደሚቆሙ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

2. ለአባላትም ሆነ ለሰራዊቱና ፖሊሱ የአክራሪዎቹ መሰረታዊ ማስፈራሪያ ወይም ክርክር ከወዲሁ የምናውቀው ነው። ይኸውም “ተቃዋሚዎች የሚፈልጉት የሥርዓት ለውጥ ብሎ ነገር፤ በዚህ ሳቢያ እኛ ደርግን ጥለን ገዢውን ፓረቲ፤ ሰራዊቱን፤ ፖሊሱን …ወዘተ በትነው፤ አባላቱን ለእስር፤ ለግድያ፤ ለረሃብ፤ ለእርዛት በመዳረግ በሕልውናቸው የሚመጣ መዓት ይሆናል” በማለት እነዚህ ወገኖች ሌላው ቢቀር፤ ለራሳቸው ሲሉ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት እንዲዋደቁ የሚሞክር አካሄድ ነው። ይህንን ይወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ፕሮፓጋንዳ ለማገዝ ካልፈለግን በሰተቀር “ወያኔ/ኢህአዴግን እናወድማለን” ከሚል ከአጉል ፕሮፓጋንዳ መቆጠብ ይኖርብናል። ከዚህ ይልቅ፤ አንደኛ በሕዝባዊ ሰላማዊ ትግል የስርአት ለውጥ ሲደረግ፤ በሙሰኝነትና በግፈኝነታቸው በራሱ በሰራዊቱ ከተጠሉ ጥቂቶች በሰተቀር፤ መቼም ሆነ የትም ሰራዊትና ፖሊስ ፈርሶ በሌላ እንዳልተተካና ሁለተኛ ደግሞ፤ የምንገነባው ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ እንደመሆኑ መጠን፤ ድርጅታቸውም እራሱን አድሶና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ከመቀጠል የሚከለክለው ምንም ነገር እንደማይኖር አበክረው መናገር ይኖርባቸዋል። ከዚህም ይልቅ “የመበተን” ነገር ከመጣ ያለው አደጋ ከዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በኩል የሚሰነዘር ሳይሆን “በታኞች” የሚሆኑት ዛሬ ከሕዝቡና ከሕብረተሰቡ የሚያናክሷቸውና ደም የሚያቃቧቸው አክራሪዎች ነገ ቀውጢ ሁኔታ ሲፈጠር ሃብታቸውንና ንብረታቸውን ወዳሸሹበት ባዕድ ሃገር የሚፈረጥጡት ገዥዎች እንደሚሆኑ አስረግጦ መናገረ ያስፈልጋል። ይህንን ሁሉ በመገንዘብ የወያኔ/ኢህአዴግ ግፈኛ ሥርዓት ሁሉንም ይዞ ገደል ከመግባቱ በፊት፤ እነዚህ በድርጅቱ ውስጥ ዴሞክራሲና የብሔሮች እኩልነት የሚሉ ወገኖች ከመዘግየቱ በፊት ከሕዝባዊ ትግል እንዲደባለቁ ጥሪ ማድረግ ያሰፈልጋል።

3. እርግጥ ይህ የመጭው ትግላችን ዋና ገጽታ ሆኖ የሚታይ ነገር አይደለም። በወያኔ/አህአዴግ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ትንንቅ እንደቀላል ነገር አንየው አልን እንጂ፤ የሃገራችንን እጣ ፈንታ እሱ ላይ እናንጠልጥል ማለታችን አይደለም። ወያኔ/ኢህአዴግ ተከፈተ አልተከፈተ፤ የቆየ የአጭርና የረጅም ጊዜ አጀንዳችንን አንግበን ሕዝባችንን ከዕለት ዕለት ይበልጥ ለትግሉ ባለቤት እያደረግን የምንቀጥልበት ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ፤

ሀ) በአጭር ጊዜ አንጻር፤ ፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ፤ የፕሬስ ነጻነትን የሚያፍነው አዋጅ እንዲነሳ፤ በጸረ ሽብር ትግል ስም ማንኛውንም ሕጋዊና ሰላማዊ ተቃውሞ ለማፈን የሚጠቀሙበት ጸረ ሽብር አዋጅ እንዲሻር፤ የሲቪክ ማህበራትን ለማኮላሸት ተጠንስሶ፤ በእርግጥም በሀገራችን በዚህ መስክ በቅድመ ግንቦት 97 ወቅት በስንት መስዋዕትነት የተገነባው ሁሉ የፈራረሰበት ሁኔታ ውስጥ ስለሆንን፤ እነዚህን ጥያቄዎች አንግቦ በውስጥም፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም በአንድነት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ለ) ወደምንፈልጋት አዲስ ኢትዮጵያ የሚደረገው የትግል ጉዞ ወሳኝ ምዕራፍ የሚደርሰው ለዴሞክራሲ የሚደረገው ሕዝባዊ ትግል አይሎ ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባዔ ሲሰየም እንደሆነ፤ ተደጋግሞ ተገልጿል። ይህ አገር አቀፍ የሽግግር ጉባዔም በሕዝብ ትግል በውስጡ ዴሞክራሲያዊ ተሃድሶ ማካሄድ መገደድ የሚኖርበትን ወያኔ/ኢህአዴግንም ጨምሮ፤ በሀገርም ሆነ በውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሲቪክ ማህበራትና ስብስቦች፤ የሙያ ማህበራት፤ የምሁራን፤ የወጣቶች፤ የሴቶችና ሌሎች ማሕበራት ተወካዮች እንዲሁም ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚጋበዙ የሃገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች የሚገኙበት እጅግ ሰፊ ጉባዔ ይሆናል።

ሐ) ከፍ ብለን እንደጠቆምነው እነዚህን የአጭርና የረጅም ጊዜ አጀንዳዎች ዕውን ለማድረግ በሕዝባዊ ትግል የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ከጥፋት ሂደታቸው እንዲገቱ ማድረግ የማይታለፍ ግዴታ ነው። ለዚህ ደግሞ ቀደም ብለን በጠቀስነው በኢዴሃህ ሰነድ በቀረበው መልክ፤

- ዛሬ በሕብረተሰባችን አስከፊ የሆነ ጨለምተኝነት ነግሷል፤ ትጥቅ መፍታት አለ፤ ተቃዋሚ ጎራ በሕዝባችን ፊት ጨርሶ ተአማኒነት አጥቷል ከሚለው ሃቅ ተነስቶ፤ ይህንን ለመወጣት ምን አጀንዳ ይዘን እንንቀሳቀስ? ይህ ትግል ከተሳከልን ደግሞ እንደገና በሽብርና በወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ መልሶ እንዳይፈታ ምን እናድርግ?
- በሀገር ውስጥም ቢሆን ቀጣይነት የሚኖረው ሕዝባዊ የትግል እምርታ ለመፍጠር በሕጋዊነት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካም ሆነ የሲቪል ሶሳይቲው ድርጅቶች ባሉበት እጅግ ፈታኝ ሁኔታም ውስጥ ሆነው፤ ለትግሉ ከአሁኑ ይበልጥ የሚያመረቃ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ፤ በሚያነግቧቸው መፈክሮችም ሆነ ባደረጃጀታቸው ይበልጥ ብቁ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ እንዴትና ምን ማድረግ ይቻላል? ትግላቸውንስ በምን ዘዴ ልንረዳ እንችላለን?
- በሀገር ቤት ሕዝባዊ ትግሉን ለመቀስቀስም ሆነ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ሁሉም ብሶቱን አንግቦ እንዲንቀሳቀስ፤ ሁሉም ብሶትህ ብሶቴ ብሎ እንዲተጋገዝ፤ ሁሉም ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት ያለው አንድ አማራጭ የሥርዓት ለውጥ መሆኑን አምኖ፤ ለዴሞክራሲ ዕውንነት በአንድ አቅጣጫ እንዲገፋ ብለን በሰነዱ ለጠቀስነው “ሶስትዮሽ” ስትራቴጂ ዕውንነት በወጣቱ፤ በሰራተኛው፤ በገበሬው፤ በነጋዴው፤ በኢንቨስተሩ፤ በሴቶች፤ በመንግሥት ሰራተኞች፤ በሥራ አጦች፤ በጎዳና ተዳዳሪዎች፤ … ወዘተ ዙሪያ አንቀሳቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ግንባር ቀደም ሃይሎች አስተማማኝ የሆነ የሕቡዕ ታግሎ አታጋይ መዋቅር እንዲዘረጉ በምን ዘዴ ልንረዳ እንችላለን?

እነዚህ ሁሉ እጅግ ውስብስበ የሆኑ ጥያቄዎች የግል ድርጅትን ሳይሆን፤ ሕዝብንና ሃገርን በሚያስቀድም መልክ በሚካሄዱ ውይይቶች መቋጠር ይኖረባቸዋል። ከዚህ ውይይት የጋራ ትግል ማኒፌስቶ ማጽደቅና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ አሁን ባሉት ስብስቦች ትብብር የጋራ ታግሎ አታጋይ አካል የመፍጠሩ ጉዳይ ትኩረት የምንሰጠው ሀገራዊ አደራ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ዛሬ ለሕዝብና ለኢትዮጵያ እንቆማለን የሚሉ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድርጅቶች አንገብጋቢና አጣዳፊ ተግባር እንዲህ ዓይነቱን ውይይት እያበራቱ ወደ አንድ የጋራ መፍትሄ የምንሄድበተን ጎዳና ማዘጋጀት ይመስለናል። በዚህ በኩል ድርጅታችን በአባልነት የሚሳተፍበት “ የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎም” ሆነ ከሌሎች ስብስቦች ጋር በመተባበር የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን እናረጋግጣለን።